# አገርን ከጥፋት ማዳን ዋና አላማነት እና የሶሪያና የዩጎዝላቪያን ተመክሮ መውሰድ

*መንግስቱ ሙሴ/ዳላስ*

አንባ ገነኖች የትም አገር ይፈጠሩ የት ይኑሩ ያላቸው ባህርይ አንድ ነው። ዘመን ሲፈጠር ጀምሮ የሰው ልጅ ለእራሱ በማሰብ ሌላው ወገኑን ማጥፋት የራሱን ሰላም ማሳጣት መሆኑ አይገባውም እና ታሪክን ሽህ ግዜ ይደጋግማታል። የሌላውን አንባገነን ስራ እና ጥፋት መልሶ ሲደግም ማየት የተለመደ ነው።

የአረብ አብዮት የተባለው የቅርብ ግዜ አብዮት መሰረታዊ አነሳሱ ለረጃጅም አመታት በህዝብ ጫንቃ ላይ ተቀምጠው የገዙትን የአረብ አንባ ገነኖች የማስወገድ ሕዝባዊ አብዮት ነበር የተካሄደው። እንዳየነውም ሁሉም አንዱ ከሌላው ተምሮ ለሀገር እና ለእራሱ ንኳን አስቦ ስልጣንን ሕዝብ በተመኘው ስርአት እንዲተዳደር በሰላም አላሳለፈም። የልቅም ሕዝብን ለማቸነፍ እና የቀራጭ ፈላጭ ስልጣን እንደነበረ ለማስቀጠል የሚችለውን ሁሉ አደረገ። ሳዳም ሆሴን እና ሞሀመድ ጋዳፊ ለሁለት ትውልድ የገዟትን አገራቸውን እና ሕዝባቸውን በሰላም አደላድለው ስልጣን ሽግግር አድርገው ሳይሆን ያለፉት የገዟትን ሀገር በተለያዩ ኃይሎች እንድትፈርስ እና የአውሬ መኖሪያ እንድትሆን. ለዘመናት የገነቧቸውን የኢኮኖሚ አውታሮች እንኳን ብትንትናቸው እንዲወጣ አድርገው የኋላ ኋላ እነሱም የውሻ ሞት የሞቱ ክፉ አንባገነኖች ነበሩ። እነሱ ገንብተው ያፈረሷት ሀገራቸው እኔ ከሞትሁ ሰርዶ አይብቀል በሚያሰኝ ለዘላቂው ከባድ ችግር ለህዝባቸው እና ለሀገራቸው ጥለው አልፈዋል።

ተመክሮ ከሶሪያ አብዮት

እንደሚታወቀው የአውሮፓ ቅኝ ገዥወች የሦስተኛው አለም እየተባለ የሚጠራውን የደቡባዊ የአለምን ክፍል በቅኝ ግዛት ሲይዙ እንደመሰረታዊ ታክቲክ የተጠቀሙበት ተወላጅ ዜጎችን ለቅኝ ገዥው እንደራሴ ሆነው እንዲያገለግሉ በማድረግ ነበር። እናም እንዲህ አይነት ሰወች የሚመለመሉት አንድም አናሳ ከሆኑ እና ከተናቁ ከተዋረዱ የሀገሪቱ ክፍል አለያም ቅኝ ገዥወች መልምለው እና በእራሳቸው አስተዳደር እና ስርአት አሰልጥነው በማስቀመጥ ነበር። ሶሪያን በቅኝ ይዛ ለብዙ ዘመን ያተዳደረችው ፈረንሳይ ለቅኝ ግዛቷ እንዲመች በማሰብ ወታደራዊ እና የሀገሪቱን ተቋማት የሞላችው አናሳ ከሆነው ከአላዋይት ሴክት በመመልመል ነበር። በ1963 እ ኤ የሶሻሊስት ባዝ ፓርቲ ሲቋቋም ድርጅቱ ከሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች እንዲሰባጠሩበት ከተደረገ በኋላ በዋነኛነት ግን አናሳ የሆነው የአላዋይት ሴክት አባላት ከፍተኛ የፓርቲውን ተቋማት ንዲቆጣጠሩት ሆነ። በ1966 የስድስት ቀን ጦርነት እየተባለ የሚታወቀው እና ጽዮናዊት እስራኤል ሀያል ሆና የወጣችበት መላ የአረብ አገራትን የጦር ግንባር ያቸነፈችበት ከመጀመሩ ቀደም ብሎ ሶቪየት ሕብረት ወደ ሶሪያ ገባች። በነበረው አለማቀፍ የኃይል አሰላለፍም የሶሻሊስቱ ባዝ ፓርቲ ወደኮሚኒስትነት እንዲቀየር በመደረጉ ፓርቲው በውስጥ ስትራክቸሩ የአላዋይት የበላይነትን ይዞ ግን ሁሉን አቀፍ በማስመሰል ወደመንግስት ስልጣን ለመምጣት ችሏል። እናም የአላዋይት የፖለቲካ የበላይነት በ ሀፌዝ አላሳድ 1966 ይጀምራል። ሀፌዝ አላሳድ ሀላዊት ሲሆን በ1966 የሶሪያ የጦር ሀይሎች የበላይ ኤታማጆር ሹም እና የመከላከያ ሚኒስቴር ሆነ። የአረቡ አለም መሪ ተብሎ የሚታወቀው የግብጹ ጀማል አብደል ናስር 1970 ከሞተ በኋላ ሀፌዝ አላሳድ ወደ ሶሪያ የስልጣን ቁንጮ በማምራት የጠቅላይ ሚኒስቴርነት ስልጣኑን እና የአረቡ አለም መሪነትን ወሰደ። በ1966 በስድስቱ ቀን ጦርነት ከአረቦች የተወዱ ቴሪቶሪወችን ለማስመለስ ብሎም እስራኤልን ከምድረ ፍልስጤም ለማጥፋት በሚል እቅድ አረቦች ዳግም የጦርነት ጥሪ ለአረቡ አልም ሲያቀርቡ አሳድ የዚህ ግንባር ዋነኛው መሪ ሆነ። የጥቅምቱ ጦርነት እየተባለ የሚታወቀው ከኦክቶበር 6 እስከ ኦክቶብር 24 1973 በጽዮናዊቷ እስራኤል እና በቀሪው የአረብ አለም መካከል የተደረገው በእርግጥም የተመራው በሀፌስ አል አሳድ ነበር። ያተጋድሎ ብዙ የፍልስጤም ታጋዮችን ያስበላ

እንድ በአረቦች ሽንፈት የተቋጨ የታሰበውን የሲኒያን፣ እና የጎላን ከፍታ ድንበርን ያላስመለሰ ፍልስጤማውያንን ዳግም ለስደት የዳረገ ጦርነት ነበር።
በሶሪያ በባዝ ሶሻሊስት ፓርቲ የበላይነት የአላዋይት የአናሳ የበላይነት ከተንሰራፋ በኋላ ሀፌዝ አላ ሳድ እስከ ህይወቱ ፍጻሜ ማለትም እስከ 2000 አ አኤ አ ስልጣን ላይ ቆይቶ ሲሞትም ለልጁ ስልጣኑን አውርሶ አልፏል። ይህ የሚያሳየው በአንድ ሀገር ከአናሳ ህብረተሰብ የወጡ አንባ ገነኖች እስከህልፈታቸው ስልጣንን ለመልቀቅ ፈቃድ የማይሰጡ ብሎም ከሀገር በላይ የነሱ ስልጣን ዋነኛ መሆኑን እና ጎሳወቻቸውን በማስፈራራት፣ በማስጠንቀቅ እስከመጨረሻ ሁሉም እንዲሰዋ እንጅ ለህብረተሰብ ለውጥ ቦታ እና እድል እንዲኖረው አይፈቅዱም።

ሶሪያ ዛሬ
ሶሪያ ፈርሳለች። አሁንም በዚህ ሰአት አንባገነኑ የአናሳ ቡድን አሳድ ስልጣን ለመልቀቅም ሆነ ወደመሀል መጦ የሽግግር መፍትሄ ለመሆን ፈቃደኛ አይደለም። በሌላ በኩል የሶርያ አገራዊ ኳላዊነት ተደፍሮ አራት ሀይሎች ከውጭ ደጋፊወቿቸው ጋር እየተርመሰመሱባት ይገኛል። የአላዋይቱ የአሳድ መንግስት የሚመራው ጦር በኢራን እና ኢራቅ መንግስታት በመደገፍ፣ የኢራቅን እና የኢራንን ልዩ ጦር በማስገባት እየታገዘ ውጊያውን ቀጥሏል። ይህ ቡድን 11 የጦር ሬጅመንቶች ይዞ ይንቀሳቀሳል። እነዚህ ሬጅሜቶች የአየር፣ የምድር ኢንፋንተሪ፣ የኮማዶ፣ የሜካናይዝድ ብርጌድ ኢንፋንተሪ፣ የከባድ መሳሪያ ወዘተ ሲያካትት። ከውጭ ከላይ እንደጠቀስኩት የኢራቅ ጦር፣ የኢራን ጦር፣ የራሽያ ጦር፣ የደቡብ ኮሪያ ጦር፣ እና የቻይና ድጋፍን ይይዛል።

ሁለተኛው ግሩፕ Syrian Free Men Force በሚል የተደራጀ እና በአቅሙ መለስተኛ የሆነ ሲሆን ይህ ቡድን የሁሉም የአውሮፓ አገራት ድጋፍ ከሳውዲ አረቢያ እና ካታር ጀርባ በመቆጥም ያገኛል። የሚዋጋው ለግዜው የሳዳትን አላዋይት ብሄረሰብ ነው። ሌላው ለመጀመሪያ ግዜ ከሁለተኛው የአለም ጦርነት በኋላ እና በይበልጥም ከሰሜን አትላንቲክ የጦር ቃልኪዳንንነት ወጣ በማለት የቱርክ የጦር ኃይል በዚህኛው ክፍል ተጠቃልሏል። ይባስ ብሎ ቱርክ የዚህ ቡድን አቸናፊነት እያጠራጠራት በመምጣቱ ከሩሲያ ጋር ንግግር መጀመሯ እና ምናልባትም የአሳድ ኃይል አሸናፊ ሆኖ እንዲወጣላት ዝንባሌ ማሳየቷ አልቀረም።

ሦስተኛው ክፍል ትልቁ የተቃዋሚ ክፍል ሲሆን የሶሪያ ዴሞክራትክ ሃይሎች ይባላል። ይህ አሜሪካ በግንባር ቀደምትነት የምትደግፈው እና መላ የምእራብ አውሮፓ ሀገራት ፋይናንስ የሚያደርጉት ክፍል ነው። በዚህ ክፍል ከሁለተኛው የሚለየው የከርድስታን ሀይል PKK የሚባለው እና በቱርክ እንደዋና ጠላትነት የሚቆጠረው የጦር ኃይል አለበት።

አራተኛው ክፍል የካሊፋት ኃይል የሚባለው በእንግሊዘኛ ምህጻረ ቃሉ ISS Islamic State of Iraq and the Levant የሚባለው ኃይል ሲሆን ቀላል የማይባል ጉዳት እያደረሰ መሆኑ እና ከጀርባው በግልጽ የሚታወቁ ሃገራት ባይኖሩም በሎጅስቲክስ ከሌሎች ተመጣጣኝ አቅም ይዞ የሚንቀሳቀስ ነው።

ባጭሩ አናሳ አንባ ገነኖች ስልጣን ከያዙ በኋላ ሀገርን እና ሕዝብን የኔ ይሆናሉ ብሎ ማሰብ የሚሳናቸው ስለሆኑ ስልጣናቸው በአይናቸው ላይ እየጠፋችም ትግላቸውን እራሱ ተንገድግዶ እስኪያቆም ይቀጥሉበታል። ይህ አባባል ዛሬ በሶሪያ እየተካሄደ ላለው እውነታ አመላካች እና ጥሩ ምሳሌ ሲሆን ይህን አደጋ በሀገራችን እንዳይከሰት ግን ሙሉ ለሙሉ በተቃዋሚው እና በተለይም የህወሓት ፈርሰ ሆነው ለአለፉት 27 አመታት ያገለገሉ አራት አባሮቿ ላይ ይወድቃል።

እንደምናውቀው በአዴን የተባለው (የብሄረ አማራ) ብሎ እራሱን የሰየመ ቡድን ምንም እንኳን የዝቅተኛ አባላቱ ከክልሉ የተወለዱ እና የአካባቢ ውጤቶች እንኖር ብለው ያደሩ ይሁን እንጅ የበላይ አመራሩ ከአመሰራረቱ ጀምሮ በህወሓት አባልነት እና በዘር እምነታቸው ከወያኔዋ ጋር አንድ የሆኑ ናቸው። ስለነሱ ለአመታት የተባለ ስለሆነ እንደነሱ ዘር እና አጥንት እየቀጠርን

ማስረዳት የለብንም እና ቃል ከዚሁ ከፌስቡክ ልዋስ እና የቁጩ አማራ ድርጅት መሪወች ይህ ለአደጋው መድረስ ዋነኞቹ እንጅ ተጠቂወቹ እንዳልሆኑ ልንገነዘብ ይገባል።
ለውጥ አይቀሬ ነው። ለውጡን ለማምጣት በሚደረገው ግብ ግብ ግን ከላይ ለማሳየት የሞከርኩትን የውጭ ጣልቃ ገብነትን እና የህወሓትን የውጊያ ዘመን ለማሳጠር ብሎም ለመግታት ተቃዋሚው ከመቸውም የበለጠ ወደ እራሱ መመልከት ብሎም ከትንሽ እስከ ትልቅ (ትልቅ ካለ) ወደአንድ መምጣት የግድ ይላል።

ዛሬ እንደምናየው ወያኔ ብሄራዊ መግባባትን ከአፍ ውጭ ልትተረጉም እንደማትችል፣ ተፈጥሮዋም ሊፈቅድላት እንደማይችል በዚህች በአጭር መጣጥፍ ለመጠቆም ሞክሬአለሁ። በተቃዋሚው መሀል የበሬ እንትን ይወድቅልኛል ብላ ተከተለች እንደሚባለው ተረት ሁሉ አሁንም ህወሓት በሀገሪቱ እና ሕዝባችን ላይ ያንዣበበውን ከባድ አደጋ ፈጣሪ እንጅ የመፍትሄው አካል ልትሆንም ሆነ ሊታሰብ የማይገባው መሆኑን ማወቅ። ብሎም ድርድር ምንጥስ የሚባል ቧልትን ትቶ ከሌሎች ተቃዋሚ ኃይሎች ጋር ለመስራት መነሳት ይኖርባቸዋል። በይበልጥም ለአለፉት 40 አመታት ታሪክ እንደምናውቀው ህወሓት መታመን አይደለም ህወሓት ጠፍታም ትነሳለች ብሎ ማሰብ እና መስራት ይኖርብናል። ሀገር ከምንሰማቸው የጥፋት ጎዳናወች ትድን ዘንድ የተቃዋሚ አንድነት ከአፍ የዘለለ መሆን አለበት አለበለዚያ ያው የህወሓትን ጎዳና የተከተለ ነው። ለጥምቀት ያልሆነ ቀምሲ ይ--- ይባላል እናም የተያዘውን ህዝባዊ ትግል የማይደግፍ ማንም የተቃዋሚ ኃይል ከህወሃት የተሻለ እንዳልሆነ ሁሉ ቢጠፋ ይሻላል።

ሀገራችን አደጋ ላይ ናት ስንል የእራስ ቤትን እስኪያንኳኳ ማለት አይደለም። ወገኖቻችን በአውሬ መንግስት ንኝ ባይ ደማቸው እየፈሰሰ ነው። አምና በባሕርዳር ያየነው የደም ጎርፍ ሰሞኑን በወልድያ እና በቆቦ ተደግሟል፣ በጨለንቆ ተደግሟል፣ በሻምቦ እና አንቦ ተደግሟል። ጎንደር ላይ የሚፈሰው ደም ከህወሓት አዲስ አበባ መያዝ ጀምሮ አላቆመም። ስለሆነ ህዝብን ማገዝ ከህዝብ ጎን መቆም የተደራጁ ኃይሎች አላማ መሆን አለበት። ትብብር ከምንግዜውም በላይ አንገብጋቢ ነው። ትግሉ በአንድ አላማ እንዲሰለፍ እና አንድ አቅጣጫ እንዲኖረው ያስፈልጋል። የሎጅስቲክስ ነገር እጅግ አንገብጋቢ ጥያቄ ነው። በተናጠል እየታገለ በመሞት ላይ ያለ ሕዝባችን የአስፈላጊ ቁሳቁስ እና መድሀኒት አቅርቦት እንኳን የለውም። ስለሆነም በአንድ ወደአንድ በመለስተኛ አላማ መሰባሰብ እና ትግሉን መምራት መቀላቀል ይጠበቃል። ከውጭ ልክ እንደ 1966-78 ዓም ሁሉ መግባት ሊታገሉ የሚችሉ ሁሉ እንዲቀላቀሉ ሊሆን የሚችለው የተቃዋሚው ወደ አንድ መሄድ እውን ሲሆን ብቻ ነው። ኢትዮጵያን ማፍረስ የወያኔ የመጀመሪያ እና ዋና አላማ ነው። ይህን ለማስፈጸም የህወሓት ክንድ እንኳን ቢዝል የአልበሽር የሱዳን ጦር በተጠንቀቅ ላይ መሆኑን ልናውቅ ይገባል። ይህ ማለት ትግሉ ሊረዝም እንደሚችል ማወቅ፣ መገመት እና በጋራ መዘጋጀትን ይጠይቃል። ህወሓት የዝር ማጥፋት ስራ እያካሄደች ነው። የተደራጀ ሀይል በአንድ ከቆመ ይህ አሁን በማህበራዊ ገጾች የምናየው ያልተሟላ የዜና ስርጭት መልክ ባለው እና ለአለማቀፍ በሚደርስ መልኩ ሊተገበር ይቻላል።

Laub, Z. (2017). *Who's who in Syria's civil war*. Retrieved January 25, 2018, from
https://www.cfr.org/backgrounder/whos-who-syrias-civil-war

ኢትዮሚድያ - Ethiomedia.com
January 31, 2018